# የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ጉዳይ!!!!!!!!!

በአብይ ጨልቀባ*

## መግብያ

በቅርቡ በተለያዩ የአዉሮፓ እና የአሜሪካ አገራት የሚገኙ የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭን በመቃወም የተለያዩ ሰለማዊ ሰልፎችን አካሂደዋል፡፡ የቦንድ ሽያጭ ሂደቱ በማወክ በተወሰነ ሁኔታ ተሳክቶላቸዋል፡፡ ከዚህ ባለፈም ራሱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት ብሎ የሚጠራ የአባይ ቦንድ ሽያጭ ህገ ወጥ ነዉ በማለት ጭምር በቦንዱ ላይ ያነጣጠረ አቤቱታ ለአሜሪካ የገበያ ልዉዉጥ ኮሚሽን አቅርባል፡፡ መቃወም መብት ቢሆንም የተቃዉሞ ይዘት እና አይነት ማወቅ ግን ጠቀሜታ አለዉ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተቃዉሞዎች እኩል አይደሉም፡፡ ሁሉም ተቃዉሞዎች ተመሳሳይ ይዘት እና ቅርፅ የላቸዉም፡፡ ሁሉም ተቃዉሞዎች ተመሳሳይ ዉጤት የላቸዉም፡፡ ሁሉም ተቃዉሞዎች አይጠቅሙም፡፡

## የፕሮአክቲቭ እና ሪአክቲቭ ተቃዉሞዎች ፍልስፍና

እንዳንድ ተቃዉሞዎች የፕሮአክቲቭ (proactive) ባህሪ የተላበሱ ናቸዉ፡፡ አንዳንድ ተቃዉሞዎች ደግሞ ሪአክቲቭ(reactive) ባህሪ አላቸዉ፡፡ ምንም እንኳን ፕሮአክቲቭ እና ሪአክቲቭ ተቃዉሞዎች ቢሆኑም ሁለቱም ግን የየራሳቸዉ መገለጫ ባህሪ አላቸዉ፡፡ ዉጤታቸዉም ቢሆን የተለያየ ነዉ፡፡ የፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ መሰረታዊ መለያዉ አጀንዳ መቅረፅ ያደረገ ሲሆን በተከላካይነት ወረዳ ሳይሆን በአጥቂነት መስመር የሚመደብ ነዉ፡፡ ይህ ተቃዉሞ የፓለቲካ ግብን የማሳካት አቅሙ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ለፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ የፓለቲካ ጎል የማስቆጠር ስራም ቀላል ነዉ፡፡ በተቃራኒዉ ሪአክቲቭ ተቃዉሞ አጀንዳ መቅረፅን መሰረት ያደረገ ሳይሆን በፕሮአክቲቭ ሃሳብ ባስነሱ ሃይሎች ላይ በመንጠልጠል በዜሮ ለማባዛት መሞከር ማለት ነዉ፡፡ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ አዳዲስ ሃሳቦች የማመንጨት አቅሙ እንዲሁም ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚጫወተዉ ሚና በጣም አናሳ ነዉ፡፡ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ የፕሮአክቲቭ ሃይሎች ጭራ እየተከተሉ አዲስ ሃሳብ ሳያፈልቁ ግን የተነሳዉን አዲስ ሃሳብ ለማፍረስ የሚሞክር ብቻ ነዉ፡፡ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ አስተሳሰብ ተከታዮች የፓለቲካ ማኖ የመንካት ተጋላጭነት ከፍተኛ ነዉ፡፡ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ የፓለቲካ ተመልካች(audience) የመሳብ አቅሙም ቢሆን አናሳ ነዉ፡፡

ከሌላ አቅጣጫ ስናየዉ ደግሞ በፕሮአክቲቭ እና ሪአክቲቭ ተቃዉሞዎች መካከል ያለዉ ልዩነት መሰረታዊ መፍትሄ ላይ ለመድረስ መሰረታዊ ችግር እና የችግሩ መገለጫ ጠንቅቆ የመረዳት ያለዉ ችሎታ ነዉ፡፡ ፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ የችግሩን

** አቶ አብይ ጨልቀባ በአምቦ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸዉ፡፡ በኢሜይል አድራሻቸዉ chewabiy@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡

ምንጭ(the root cause of the problem) የመረዳት ችሎታ አለዉ፡፡ ሪአክቲቭ ተቃዉሞ ግን የችግሩ መገለጫዎች (symptoms of the problem) ላይ ነዉ የሚያነጣጥረዉ፡፡ለምሳሌ በተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎች የሚገኙ የመንግስትን ስልጣን መቆጣጠር ለምን እንዳልቻሉ በምክንያትነት የሚያቀርቡት የመንግስት ስልጣን የተቆጣጠረዉ የፓለቲካ ፓርቲ እንደሆነ ሊገልፁ ይችላሉ፡፡ ይሄ የችግሩ ሁኔታዎች የሚያስረዳ ነዉ፡፡ ስለሆነም በተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎች የተሰለፉት ሃይሎች ባሉበት ነባራዊ ሁኔታ የመንግስት ስልጣን የያዘዉ ፓርቲ በመዉቀስ ብቻ የፓለቲካ ኑራቸዉን ይመራሉ፡፡

በተቃራኒዉ ፕሮአክቲቭ ተቃዉሞዎች በተቋማት ወይም በገዢዉ የፓለቲካ ፓርቲ ኃይል ላይ አይደለም የሚያነጣጥሩት፡፡ ፕሮአክቲቭ ተቃዉሞዎች የሚያነጣጥሩት የችግሩ ምንጭ ላይ ነዉ፡፡ የችግሮች ምንጭ የሚገኝበት ደግሞ በሃሳቦች መሃል እንጂ በተቋሞች ላይ በማነጣጠር አይደለም፡፡ የፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ የችግሩ ምንጭ ለይቶ በተመሳሳይ አጀንዳ ቀደም ብሎ ሌላ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያቀርብ ነዉ፡፡ ለምሳሌ አንድ የልማት ፕሮጀክት የተቃዉሞዉ ፍሬ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ በፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ መሰረት የልማት ፕሮጀክቱ የሚገነባዉ ድርጅት ወይም የፓለቲካ ፓርቲ መሰረት ያደረገ መሆን የለበትም፡፡ ምክንያቱም በተቋሞች ላይ ማነጣጠር መሰረታዊ አማራጭ መፍትሄ ሊያሳይ ስለ ማይችል ነዉ፡፡ በፕሮአክቲቭ ተቃዉሞ መሰረት የልማት ፕሮጀክት ተቃዉሞ ይዘት ከኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ወይም የአካባቢያዊ ብክለት እና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸዉ ምክንያቶች መሆን አለባቸዉ፡፡ የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ወይም የአካባቢ ብክለት በሁኔታዎች(circumstances) ላይ የተመሰረቱ ስላልሆኑ፡፡ የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ወይም የአካባቢያዊ ብክለት ሙጉት በሃሳብ ላይ የተመረኮዙ ናቸዉ፡፡

<u>የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ተቃዉሞ ከፕሮአክቲቭ እና ሪአክቲቭ ፍልስፍና አኳያ</u>

የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ተቃዉሞ ፕሮአክቲቭ እና ሪአክቲቭ ፍልስፍና መነፅር ማየት መሞከር ጠቀሜታ አለዉ፡፡ በአዉሮፓ እና አሜሪካ ከተሞች የተደረገዉ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ተቃዉሞ ፕሮአክቲቭ ነዉ ወይስ ሪአክቲቭ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነዉ፡፡ በተለያዩ በአዉሮፓ እና በአሜሪካ ከተሞች በተደረገዉ እና ቀጣይ ሊደረግ የሚችለዉ ተቃዉሞዎች መሰረታዊ ባህሪያቸዉ የፕሮአክቲቭ ሳይሆኑ ሪአክቲቭ ናቸዉ፡፡ አዲስ አጀንዳ የመቅረፅ ሳይሆን የተቀመጠ አጀንዳ እየተከታተሉ በዜሮ ለማባዛት ጥረት የማድረግ ስሌት ነዉ፡፡ በዲያስፖራ እና በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱት የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ስለ አባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ የተለያዩ ፍልስፍና ነዉ የሚያራምዱት፡፡ በሰላማዊ መንገድ በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች በአብዛኛዉ ጉዳይ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ ፍልስፍናን የሚከተሉ ናቸዉ፡፡ የመንግስት ስልጣን የያዘዉ ኢህአዴግ በአብዛኛዉ ጉዳይ የፕሮአክቲቭ ፍልስፍናን የሚከተል ነዉ፡፡ በሰላማዊ መንገድ በአገር ዉስጥ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች በአባይ ግድብ የቦንድ ሽያጭ በተመለከተ ግን የሪአክቲቭ ተቃዉሞ ፍልስፍና ተከታዮች አልነበሩም፡፡ ይሄ ማለት ግን

ፕሮአክቲቭ ነዉ ማለት አይደለም፡፡ቢያንስ ዝምታ ነዉ የመረጡት፡፡በፓለቲካ አይን ደግሞ ዝምታ እንደመቀበል ነዉ የሚቆጠረዉ (silence amounts to acceptance)፡፡

በዲያስፖራ መቀመጫዉ ያደረጉ አንዳንድ  የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ተቃዋሚዎች ግን የሪአክቲቭ ፍልስፍና የሚያራምዱ ናቸዉ፡፡ የሪአክቲቭ ፓለቲካዊ ፍልስፍና መንፈስ አዳዲስ ሃሳቦች የማፍለቅ አቅም የለዉም፡፡ ሪአክቲቭ እድሜ ልኩን የሌሎችን ጭራ እየተከተለ የሚኖር አስተሳሰብ ነዉ፡፡ ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች በቀላሉ ማኑፕሌት (manipulate) ማድረግ ቀላል ነዉ፤ ምክንያቱም የሪአክቲቭ ተቃዉሞ  ፍልስፍና ተከታዮች ለማኑፕሌሽን (manipulation ) ተጋላጭ ናቸዉ፡፡ የሪአክቲቭ ተቃዉሞ  ፍልስፍና አራማጆች ስሜታዊነት(emotional) ስለ ሚያጠቃቸዉ ጭምር ነዉ፡፡ ስለሆነም የፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች፤ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ እና ሌሎች ጉዳዮችም በተከላካይነት ወረዳ ነዉ የሚገኙት ምክንያቱም የሪአክቲቭ ፍልስፍና ወደ አጥቂነት መስመር የማሽጋገርያ ድልድይ ለመሆን ስለማይችል፡፡ የሪአክቲቭ ፍልስፍናን በመከተላቸዉ ምክንያት የፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ ቀርፆ  የሰጣቸዉ አጀንዳ እንደ ቤት ስራ ተቀብለዉ እየሰሩ መሆናቸዉ የገባቸዉ አይመስልም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአባይ ግድብ እየገደበ ያለዉ በኢህአዴግ የሚመራዉ መንግስት ስለሆነ መቃወም አለብን ከተባለ፤ በተቋም እንጂ በሃሳብ ላይ የተመሰረተ ተቃዉሞ አይደለም፡፡ ተቋዉሞዉ እጁን በተቋም ላይ ያነጣጠረ ስለሆነ የተቃዉሞዎዉ ይዘት ሪአክቲቭ ነዉ፡፡ የአባይ ግድብ መገደብ የሌለበት ለኢኮኖሚዉ አዋጭ ስለአልሆነ ነዉ፤ ከተባለ ግን በሃሳብ ላይ የተመሰረተ ስለሚሆን የተቃዉሞዉ ይዘት ፕሮአክቲቭ ይሆናል፡፡ ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች የያዙት አቋም ግን በሃሳብ ላይ የተመረከዘ ሳይሆን ተቋም ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡  የተለያዩ ፓለቲካ ፓርቲዎች የህዝብ ተቋማት (Public institutions) ናቸዉ፡፡ የፓለቲካ ፓርቲዎች የግለሰብ ተቋማት አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ የፓለቲካ ፓርቲዎች  የሚደግፍቸዉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ስላላቸዉ፡፡ የገዥዉ ፓለቲካዊ ፓርቲ ከሌሎች የሚለየዉ በደጋፊዎች ቁጥር እንጂ ሁሉም ፓለቲካ ፓርቲዎች የህዝብ ንብረት ናቸዉ፡፡  ኢህአዴግ አንድ የህዝብ ተቋም ነዉ፡፡ ተቃዉሞዉ በተቋም መሰረት ያደረገ አስተሳሰብ ነገ ኢህአዴግን የሚተካዉ ሌላ ፓርቲ ከመጣ ዞሮ ዞሮ ግድቡን መቃወም ይቀጥላል ምክንያቱም በሪአክቲቭ ፅንሰ ሃሳብ መሰረት ስለ ሚመራ፡፡ ስለሆነም በተቋም ብቻ ተመርኩዞዉ የአባይ ወንዝ ግድቡ መቃወም ከፓለቲካዊ ጥቅሙ ጉዳቱ ነዉ የሚያመዝነዉ፡፡

ኢህአዴግ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ተቃዉሞ ጋር በተያያዘ ሁለት ፓለቲካዊ ትርፎች ያስገኙለታል፡፡አንደኛዉ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ  የኢትዮጵያ የፓለቲካ ምህዳር አጀንዳ ሁኖ እንዲቀጥል ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች የራሳቸዉ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡  ኢህአዴግ ከሌሎች የፓለቲካ ድርጅቶች የንፅፅር ብልጫ (comparative advantage) ያለበት ቦታ የልማት ጉዳዮች አንዱ ነዉ፡፡ የአባይ ግድብ ግንባታ ደግሞ ደረቅ ፓለቲካ አይደለም፡፡ የአባይ ግድብ ግንባታ የልማት አጀንዳ ነዉ፡፡ ከኢህአዴግ የተለየ የፓለቲካ አስተሳሳብ ያላቸዉ ድርጅቶች የልማት ጉዳይ

ከኢህአዴግ በላይ የንፅፅር ብልጫ ሊኖራቸዉ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የልማት ጉዳዮች ኢህአዴግ በብቸኝነት የተቆጣጠረዉ ቦታ ስለ ሆነ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በልማት ጉዳዮች ኢህአዴግ በጣም ከተሳኩለት ቦታዎች አንዱ ስለ ሆነም ነዉ፡፡ ኢህአዴግ የንፅፅር ብልጫ ባለበት ቦታ የኢትዮጵያ የፓለቲካ ምህዳር አጀንዳ ሁኖ እንዲቀጥል በማድረግ ከኢህአዴግ ለየት ያለ የፓለቲካ አስተሳሰብ የሚከተሉ ድርጅቶች የሚጠቅማቸዉ አይደለም፡፡ በዋናነት ደግሞ የፅንፈኛዉን የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች የሚጎዳቸዉ ነዉ፡፡ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ መቃወም በተዘዋዋሪ የኢህአዴግ የንፅፅር ብልጫ  አጀንዳ ማስተዋወቅ ማለት ነዉ፡፡ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭን የአገር ዉስጥ አጀንዳን መሆኑ ብቻ ቀርቶ አለም አቀፍ አጀንዳ እንዲሆን  ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ግድቡን የማስተዋወቅ ስራ እየሰራ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ዙሮ ዙሮ ተቃዉሞዉ አዲስ አጀንዳ የመቅረፅ መንፈስ የለዉም፡፡ ሌላ አካል የቀረፀዉ አጀንዳ በዜሮ ለማባዛት መሞከር ወደ አጥቂነት አያሸጋግርም፡፡

ሁለተኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎችን  የሚጠራጠርበት መንፈስ የሚያጠናክር ነዉ፡፡ ፅንፈኛዉ ዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች  ከኢትዮጵያ ህዝብ  ለመለያየት ኢህአዴግ የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭን ከሰማይ እንደ ወረደ መና ሊቆጥረዉ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢህአዴግ ለ23 ዓመታት ስልጣን ላይ የቆየበት ዋነኛዉ ሚስጥር የፓለቲካ ዲስኮርስ (discourse) የመቀየር ችሎታዉ ነዉ፡፡ የፓለቲካ ዲስኮርስ መሰረቱ ፕሮአክቲቭ ፍልስፍና ነዉ፡፡ ለምሳሌ የብሔር ፌደራሊዝም ፅንሰ ሃሳብ ከማስተዋወቅ ጎን ለጎን የአገሪቱም አንድነት የሚያጠናክር የፓለቲካ ዲስኮርስ ባለፉት አስር አመታት ለህዝቡ አስተዋዉቃል፡፡ የባንዴራ ቀን እና የአባይ ግድብ አዲስ የፓለቲካ ዲስኮርስ ናቸዉ፡፡ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች ግን የፓለቲካ ዲስኮርስ መቀየር ተስኗቸዋል፡፡ ምክንያቱም ፅንፈኛዉ የዲያስፖራዉ ተቃዋሚዎች የፍልስፍና መሰረታቸዉ በሪአክቲቭ አስተሳሰብ የተቀረፀ ስለሆነ ነዉ፡፡ የሪአክቲቭ አስተሳሰብ የፓለቲካ ዲስኮርስ የመቀየር አቅም የለዉም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በአገር ዉስጥ በሰላም የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች የፓለቲካ ዲስኮርስ ያለመቀየር በሽታ ተጠቂዎች ናቸዉ፡፡ በአስተሳሰብ ደረጃ በዲያስፖራዉ እና በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች የፓለቲካ ዲስኮርስ መቀየር ስለተሳናቸዉ ወደ ስልጣን የሚመጡበት ጊዜ በጣም እየራቀ መጥቷል፡፡ የፓለቲካ ዲስኮርስ ያለመቀየር ምክንያታቸዉ ደግሞ የሪአክቲቭ ፅንሰ ሃሳብ ነዉ፡፡

**ማጠቃለያ**

ኢትዩጵያን ሲያስተዳድራት የነበሩት መንግስታት የአባይን ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ አድርገዉ እንደተንቀሳቀሱ ታሪክ ምስክር ነዉ፡፡ ንጉስ ኃይለ ስላሴ እና ደርግ በአባይ ዙሪያ ተመሳሳይ አቋም ነበራቸዉ፡፡ በኢህአዴግ የሚመራዉ መንግስትም በአባይ ጉዳይ ከቀደሙት ሁለት መንግስታት ጋር ተመሳሳይ አቋም ይጋራል፡፡ ስለሆነም ኢትዩጵያን የሚያስተዳድራት መልአክ ይሁን  ሰይጣን የአባይ ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብ (non-negotiable) ጉዳይ ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የአባይ ወንዝን ለመገደብ የተነሳዉ መልአክ ይሁን ሰይጣን ከመደገፍ ወደ ኃላ አላለም፡፡ ስለሆነም የአባይ ጉዳይ የመንግስታት አጀንዳ ሳይሆን የኢትዩጵያ ህዝብ ቀዳሚ አጀንዳ ነዉ፡፡ ከኢትዩጵያ ህዝብ  አቋም በተቃራኒዉ መስመር መሰለፍ ከህዝብ ጋር ያጣላል፡፡ ያዉም ይቅር የማይባልበት ሃጥያት፡፡ መንግስት እንኳን ይቅርታ ቢያድረግ ህዝቡ ይቅር የሚል አይደለም፡፡  በዉጭ የሚኖሩ አንዳንድ ዜጎች በአባይ ግድብ ላይ ያላቸዉ ተቃዉሞ ከህዝብ ጋር የሚያጣላ መሆኑን ለምን ማየት እንደታሳናቸዉ ግራ የሚያጋባ ነገር ነዉ፡፡ በዉጭ የሚኖሩ አንዳንድ ዜጎች ያላቸዉ የፓለቲካ ልዩነት ኢህአዴግን ያገኙ እየመሰላቸዉ  በአባይ ግድብ ሂሳብ ለማወራረድ መሞከራቸዉ የተሳሳተ መንገድ ነዉ ፡፡ በኢትዩጵያ ህዝብ እይታ የፓለቲካ ልዩነትን  ሂሳብ ለማወራረድ የአባይ ግድብን  እንደ መደራደርያ ካርድ አድርጎ ለመጫወት መሞከር ይቅር የማይባልበት ፓለቲካዊ ሃጥያት ነዉ፡፡ ስለሆነም የአባይን ጉዳይ ቆም ተብሎ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የአባይ ወንዝ የመገደብ ታሪካዊ ሃላፊነት  በኢህአዴግ የሚመራዉ መንግስት መሆኑ ኢህአዴግ እድለኛን ያድርገዋል፡፡ የአባይን ግድብ ግን የኢህአዴግ ነዉ ማለት አይደለም፡፡ የኢትዩጵያ ህዝብ አንጡራ ሃብት እንጂ፡፡ ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ ይኑርም አይኑርም  የአባይ ግድብ የኢትዩጵያ ህዝብ መሆኑ ይቀጥላል፡፡ የኢትዩጵያ ህዝብ ማለት በዉጭ የሚኖሩ የአባይ ግድብ እንዳይገደብ የተቃወሙትን ጭምር የሚያካትት ነዉ፡፡ ስለሆነም ድጋፍ መስጠት ባይቻልም ዝምታ የመጨረሻዉ አማራጭ ነዉ፡፡ በተቃዉሞ መቀጠል ግን ፍርዱን ለታሪክ መተዉ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ተቃዉሞ ቢኖርም ባይኖርም  ግድቡን ለመጨረስ የሚከለክል ሃይል የለምና፡፡ ታድያ ግድቡ እንዳለቀ አሁን የሚቃወሙ ዜጎች ምን እንደሚዉጣቸዉ ለማየት የነገ ሰዉ ይበለን፡፡